# 1ኛ ክፍል የውጤት/ማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ 1
# የወላጆች መመሪያ

በ1ኛ ማርክ መስጫ ወቅት፣ የ1ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለፁት ፅንሰሃሳቦች እና ክሂሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።
እባክዎ ልብ ይበሉ፦ በ በአመድማ ቀለም የታየዉ ክህሎት እና ፅንሰሃሳቦች ትምህርት ተሰጥቷል ነገር ግን በሪፖርት ካርድ ላይ ውጤት አልተጻፈም።

## የሒሳብ ትምህርት

### በአስርዮሽ/በአስር ቤት ቁጥሮችና ስሌቶች

- በአንድዮሽ፣ እና በአስርዮሽ እስከ 120 መቁጠር፣ አንዳንድ በመደመር እና መቀነስን ጨምሮ።
- እስከ 120 ያሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መጻፍ።
- ባለ 2-አሃዝ ቁጥሮችን እንደ አስርዮሽ እና አንዶች ብዛት መወከል።
- >፣ = ፣ እና < ምልክቶችን በመጠቀም ሁለት ባለ 2-አሃዝ ቁጥሮችን አወዳድር (ሪ)።
- በተሰጠ ቁጥር ላይ ፣ 10 በማስበለጥ ወይም 10 በማሳነስ ሳትቆጥር/ሪ በማሰብ/በማስላት ማግኘት።

### ስሌት እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- በ20 ቁጥር መካከል ያሉ አሃዞችን የሚከተሉትን ስልቶች በመጠቀም መደመር እና መቀነስ
  - በ መቁጠር፤
  - በዚህ መልክ አስር በማድረግ(ምሳሌ፣ 8 + 6 = 8 + 2 + 4 = 10 + 4 = 14)፤
  - ወደ አሥር ቁጥር የሚያመራ ቁጥርን በመተንተን (ለምሳሌ፦ 13 - 4 = 13 - 3 - 1 = 10 - 1 = 9)፣
  - በመደመር እና በመቀነስ መካከል ባለው ግንኙነት በመጠቀም (ለምሳሌ፣ 8+4= 12 እንደሚሆን በማወቅ፣ 12-8= 4) እንደሚሆንም ይታወቃል፤
  - ተመጣጣኝ ነገር ግን ቀላል ወይም የሚታወቅ ድምር መፍጠር (ለምሳሌ፦ 6 + 7 በመደመር የሚታወቀውን ተመጣጣኝ መፍጠር 6 + 6 + 1 = 12 + 1 = 13
- እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን በቅልጥፍና መደመር እና መቀነስ።
- እስከ 20 ቁጥር ያሉ አሃዞችን በመደመር እና በመቀነስ በሁሉም አቀማመጥ ዋጋቸው/መጠናቸዉ ያልታወቀ ያሉት/የያዘ የቃላት ጥያቄዎችን ማቃለል።
- ቆጠራን ከመደመር እና ከመቀነስ ጋር ማዛመድ (ለምሳሌ፦ በ2 ቆጠራ ላይ 2 በመደመር)።

### አለካከና አሃዝ-መረጃ

- መረጃዎችን በሶስት ፈርጅ በስዕላዊ ግራፍ እና በቁም ግራፍ ማደራጀት።
- ስለ ጠቅላላ የመረጃ ነጥቦች/ስብስብ፣ በእያንዳንዱ ረድፍ/ፈርጅ ስንት እንደሚገኝ እና በአንደኛው ረድፍ ከሚገኘው የሌላኛው በስንት እንደሚቀንስ ወይም እንደሚበልጥ መጠየቅ እና መልስ መስጠት።
- ከ20 በታች ያሉ ቁጥሮችን በመደመር እና በመቀነስ በቃላት የተጻፉ ፕሮብሌሞችን በሁሉም ቦታ ላይ ያልታወቁ ቁጥሮችን በማስገባት/በመተካት ማቃለል/መፍታት።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፦ ስነ ፅሁፍ

- ከጽሑፍ ውስጥ ስለ ቁልፍ ዝርዝሮች ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- ትረካ መልሶ መተረክ፣ ዝርዝሮቹን ጨምሮ።
- ከታሪክ ውስጥ ገጸ-ባሕርይ፣ ዝግጅትን /መቼት እና ዋና ክዉነቶችን፣ ቁልፍ ዝርዝሮች እና ሥዕላዊ መግለጫ በመጠቀም ማብራራት።
- በአንደኛ ክፍል ደረጃ አግባብ ያለዉ ዉስብስብ ጽሁፍ ከማበረታቻ እና ድጋፍ ጋር ማንበብ እና መረዳት/ማስተዋል።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፡ መረጃዊ

- ከጽሑፍ ውስጥ ስለ ቁልፍ ዝርዝሮች ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- በአንድ ጽሑፍ ላይ በሥእላዊና በሌሎች መግለጫዎች የተገለጹ መረጃዎችን እና በቃላት የተገለጹ መረጃዎችን በማነፃፀር መለየት።
- በጽሑፉ ውስጥ የቃላትን እና ሀረጎችን ትርጉም ለመወሰን ወይም ለማብራራት እንዲረዱ ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- በአንደኛ ክፍል ደረጃ አግባብ ያለዉ ዉስብስብ መረጃዊ ጽሁፍ ከማበረታቻ እና ድጋፍ ጋር ማንበብ እና መረዳት/ማስተዋል።

### መሰረታዊ ክሂሎቶች

- ስለ ማተም አደረጃጀት እና መሠረታዊ ባህርይ ግንዛቤ መግለጽ/ማስረዳት።
- የንግግር ቃሎች፣ ፊደላት/ክፍለ ቃላት፣ እና ድምፆችን (ስነ ልሳን) መረዳት/መግለጽ።
- ቃላትን በመነጣጠል/በመለየት ለክፍል ደረጃ የሚመጥን ስነ-ቃል እና የቃላት ትንታኔ ክህሎት ማወቅ እና መተግበር።
- በአእምሮ የመያዝ ችሎታ/መረዳትን ለማገዝ በትክክል በብቃት እና በማቀላጠፍ ማንበብ።

### ቋንቋ፦ የቃላት ዝርዝር ግኝትና አጠቃቀም

- በህብረት በሚደረጉ ውይይቶች መሳተፍ፡፡
- ዘለግ ባለ/በጎላ ድምፅ ከተነበበ ጽሑፍ ላይ ወይም በቃላት ወይም በሌላ ሚዲያ የቀረቡ መረጃዎችን በተመለከተ ቁልፍ ዝርዝሮችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- ቃላትን በየፈርጁ ለይ።
- አረፍተ ነገር አውደ-ንባብ በመጠቀም የማይታወቁ ቃላት ትርጉም መፍታት።

## ጽሑፍ

### ትረካ

- ክንውኖችን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ፣ እና በርካታ ክስተቶችን በዝርዝር ስለሚዘግብባቸው ትረካዎች ለመጻፍና መደምደሚያ ለመስጠት የተለመዱ ተሞክሮዎችን ማስታወስ።
- ትርጉሙን ለማስተላለፍ ስእሎችን መጨመር።

### መረጃ የሚሰጥ/ትምህርታዊ/ገላጭ

- በአነስተኛ ቡድን ለውይይት አንድ ርእስ ላይ ጥያቄ ማንሳት።
- ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ጥቂት እውነታዎችን በማቅረብ፣ እና መደምደሚያ በመስጠት፣ርእስ የሚጠቁሙ አስተማሪ /ገላጭ ፅሁፎችን መጻፍ።

### አስተያየት

- ባስተዋወቁት አርእስት ላይ አስተያየቶችን በመጻፍ፣ ወይም ስለሚጽፉት መጽሐፍ ስያሜ በመስጠት፣ እና አስተያየት መስጠትና አስተያየቱ የተሰጠበትን ምክንያት በመግለጽ መደምደሚያ መስጠት።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- በጋራ የሚካሄድ ጥናት ላይ መሳተፍ።
- በአርዕስቱ ላይ ማተኮር፣ ከአቻዎች/እኩዮች ለሚነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች መመለስ፣ እና ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመስጠት እነደአስፈላጊነቱ ጽሑፍን ማጠናከር።
- ጽሑፍ ለማዘጋጀት እና ለማሳተም የተለያዩ ዲጅታል መገልገያዎችን መጠቀም፣ ከእኩያሞቹ ጋር መተባበርን ጨምሮ።
- ከልምድ/ገጠመኝ የተገኘ መረጃ በማስታወስ/በመጥቀስ ወይም ከተሰጡ ምንጮች መረጃ በመሰብሰብ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- ሰዎችን፣ ቦታዎችን፣ ግዑዝ እቃዎች፣ እና የተፈጸሙ ድርጊቶችን በዝርዝር አግባብ የሆኑ ሃሳቦችን እና ስሜትን በመግለጽ ማስረዳት።
- ስዕል ወይም ሌላ የሚታዩ ነገሮችን አስፈላጊ ከሆነ በመጨመር አመለካከቶችን፣ አስተሳሰቦችን፣ እና ስሜቶችን ማብራራት/መግለጽ።
- ለስራ እና ለትክክለኛ ሁኔታ አግባብነት ሲኖራቸዉ የተሟሉ ዐረፍተ ነገሮችን ማፍለቅ።
- የላይኛውና የታችኛው ፊደላትን በሙሉ ጻፍ/ፊ።
- መጠሪያ ስሞችን እና የጋራ ስሞችን፣ ነጠላ ስሞች እና የብዙ ስሞችን በመጠቀም ከግሥ ጋር ማዛመድ።

## ሳይንስ

### የህይወት ሳይንስ

- ህይወት ያላቸው ነገሮች ግንኙነት/ትስስር እና ባህሪያት እና የእነርሱን ዕድገትና ህልውና የሚደግፉ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ስላላቸው ችሎታ ግንዛቤ ማሳደግ።
- እንስሳት በተክሎች ላይ ጥገኛ የሆኑበት እና አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ የሚሆኑበትን ጥቂቶቹን መንገዶች ግለጽ።
- በምርመራ በተገኘ መረጃ በመመርኮዝ ሕይወት ያላቸው ነገሮች የተሠሩት በዓይን ከማይታዩ ረቂቅ ነገሮች እንደሆነ መግለጽ።
- ህይወት ያላቸው ነገሮች በጠቅላላ የተሰሩበት ረቂቅ ነገሮች መሠረታዊ ነገሮችን ለማከናወን የሚረዳቸው እንደሆነ ማስረጃ/ማረጋገጫ መስጠት።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ስነ-ዜግነት

- ሕግ/ሥርዓት አስፈላጊነቱን አብራራ/ሪ።
- ከዩናይትድ ስቴትስ ኦቭ አሜሪካ ጋር የተገናኙ መለያ አርማ እና ልምዶችን በመለየት ትርጉማቸው ላይ ውይይት አድርግ/ጊ።
- ለአሜሪካን የፖለቲካ ሥርዓት  አስፈላጊ/ጠቃሚ ሰዎችን መለየት እና  መግለጽ።
- በቤተሰብ፣ በት/ቤት፣ እና በጎረቤት ተሳታፊ አባል የመሆንን መብት እና ሃላፊነቶች ግለጽ/ጭ።

## የኢንፎርሜሽን መሠረተ ትምህርት

- የተሰጠ/የተመደበ ወይም በግል የሚያስፈልግ መረጃ መለየት።
- የመረጃን ፍላጎት ለማሟላት ጥያቄዎችን ማዘጋጀትና ማሻሻል።
- አስፈላጊ መረጃዎችን ለማሳካት የሚቻልበትን መንገድ መለየት፣ ምንጮቹን መምረጥ እና መጠቆም/ፈልጎ ማግኘት።
- የጥናት ግኝት/መደምደሚያዎችን ለማጋራት ዝግጅት የተለያዩ ዓይነት ቅጾችን መጠቀም።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።

## ስነጥበብ

### ስነጥበብ አቀራረብና ዝንባሌ/ምላሽ

- ሠዓሊዎች/የስነጥበብ ሰዎች የሚመለከቱትን፣ የሚያዉቁትን፣ ስሜት፣ እና በሃሳብ የሚፈጥሩትን የሚወክሉበትን መንገድ መለየት እና ማወዳደር።
- ሌሎች የስነጥበብ ሰዎች ለምን ስነጥበብን እንደሚፈጥሩ ምክንያቶችን ለይ።
- የተመረጡትን ስነጥበብ ስራዎች በርዕስ-ሀሳብ/ ፍሬ ነገር፣ እና በይዘት በየፈርጁ ለይ።
- የተመረጡት የስነጥበብ ሥራዎች/ውጤቶች በፍሬ ነገር/በርዕሰ-ሀሳብ እና በይዘት እንዴት እንደሚመሳሰሉ አስተያይ/አወዳድር/ሪ።

### ስነጥበብ ፈጠራ እና ግንኙነት/ማያያዝ

- ቀለም፣ መስመር፣ ቅርጽ፣ ተክስቸር፣ እና ይዘት በመጠቀም ከምልከታ፣ ከትዉስታ እና ከሚገመተዉ በመነሳት ሃሳብን በእይታ መወከል።
- የስነጥበብ ስራዎችን ቀለም፣ መስመር፣ ቅርጽ፣ ይዘት፣ እና ቅርፀት ጥራት መዳሰስ እናም ንድፍ በስነጥበብ ስራ ላይ ያለውን መሠረተ ሃሳብ መመርመር።
- በስነጥበብ ስራዎች የግል ትርጉምን ለማስተላለፍ በመስመር፣ ቅርፅ፣ የለስላሳና የሻካራ ሁኔታ፣ ፎርም፣ ቀለም፣ እና በንድፍ መሰረታዊ መርሆዎች መገልገል።
- በጥንቃቄና በዘዴ የስነጥበብ መገናኛ ዘዴዎችን እና መሣሪያዎችን መቆጣጠር እና መጋራት። መሳሪያዎቹን፣ የሥራ ቦታ፣ እና የስነጥበብ ክፍሉን በማጽዳት አግዝ(ዢ)።
- ከለር(ቀለም)፣ መስመር፣ ቅርጽ፣ ቅንብር/ኅብር፣ ፎርም/ዓይነት እና የተመረጠ የንድፍ መርሆችን፦ ቅጥ እና ድግግሞሽ በስነጥበብ ሥራ መለየት እና መጠቀም።

## ሙዚቃ

### ሙዚቃ መጫወት

- በላይኛው፣ ታችኛው፣ እና በመካከለኛ ቅላፄ አጠቃቀም ዘምር/ሪ።
- በተስማማ እና በውስን ድምፅ ክልል ዉስጥ፣ ልዩ ልዩ አይነት ዜማዎችና የቃና ቅጦች መዘመር።
- በክፍል ውስጥ የሙዚቃ መሣሪያዎች ቅኝት እና የድምፅ ለዛ ደርዝ አስመስል/ይ (የማስመሰል ድምፅ)።

### የሙዚቃ ምላሽ/ዝንባሌ

- በመማሪያ ክፍል ውስጥ ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን በእይታ እና በድምፅ ለይ።
- ከሙዚቃ የምትሰማውን/ሚውን ድግግሞሽ እና ንፅፅር/ልዩነት ያላቸው ክፍሎችን ለይ።
- የሙዚቃ ድምፆችን አወዳድር/ሪ፦ ፈጣን/ዝግ ያለ፣ ጮክ ያለ/ለስላሳ፣ ረዥም/አጭር፣ ከፍተኛ/ዝቅተኛ።
- ከእንቅስቃሴ ጋር እና ያለእንቅስቃሴ ድምፅ የማይጨምር የማይቀንስ የሙዚቃ ምት ተጫወት/ች።
- በዘፈን/ዝማሬ ጨዋታ የሙዚቃ አሰላለፍ ተከተል/ይ።
- እቤት ውስጥ፣ በት/ቤት፣ እና በማህበረሰብ ስለ ሙዚቃ አጠቃቀም ግለጽ(ጪ)/አስረዳ(ጂ)።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች

- በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ፣ ግለሰቦች በተለያዩ ፍጥነቶች እንዴት በመማር ደረጃዎች ውስጥ እንደሚገሰግሱ/እንደሚሻሻሉ እውቅና መስጠት።
- ጡብ ጡብ ማለት፣ መዝለል፣ መፈናጠር፣ ወይም መጋለብ በመሣሠሉት የተለያዩ የችሎታ ብቃቶችን አሳይ።
- directions፣ time/speed፣ እና force የመሣሠሉ እንቅስቃሴዎችን በመፈላለግ አቀናጅ/ጂ
- ማባረር፣ማሯሯጥ፣ማሳደድ፣ መሸሽ፣ ማምለጥ/አፈትልኮ መሮጥ ተለማመድ/ጂ።

### የግልና የማህበራዊ ሃላፊነት

- በአካል እንቅስቃሴ ቦታ ከሌሎች ጋር በመቀናጀት በውጤታማነት ሥራ/ሪ።
- የማህበረሰባዊነት ስሜትን የሚፈጥር ግኑኙነቶች መገንባት እና ማጠንከር/መጠበቅ።

## የጤና ትምህርት

### የአእምሮና የስሜት ጤንነት (MEH)

- የመግባባት/የግንኙነት ስልቶችን ለይቶ ማወቅ።
- ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚከሰቱ ስሜቶችን እና አፃፋዎችን/ምላሾችን መፈተን/መመርምር።
- እንዴት ጥሩ ምርጫ/ውሳኔ ማድረግ እንደሚቻል ለይቶ ማወቅ።

### አልኮል፣ትምባሆ/ሲጋራ፣ እና ሌሎች መዳኒቶች (ATOD)

- ተገቢ የመድኃኒት አጠቃቀሞችን ለይተህ እወቅ/ቂ።
- ትምባሆ/ሲጋራ መጠቀም እንዴት ለጤንነት ጠንቅ/ጎጂ እንደሆነ ለይተህ(ሽ) እወቅ/ቂ።
- አልኮል መጠቀም በሰውነት ላይ ያለው ተጽኖ ለይተህ(ሽ) እወቅ/ቂ።

## አስተሳሰብና የአካዴሚያዊ ስኬት ክሂሎቶች

የትንተናና ትብብር **አስተሳሰብና የአካዴሚያዊ ስኬት ክሂሎቶች** በትምህርት ዉስጥ ተካተዋል።

**ትንታኔ**— ሙሉ የሆነን አካል ወዲያውኑ በማይስተዋልበት ሁኔታ በክፍልፋዮች ማስቀመጥ እና የሙሉውን/የአጠቃላዩን አወቃቀር/ቅርጽ ለመረዳት ክፍልፋዮቹን መመርመር።

- መለያ ባህርያትን መለየት እና መግለፅ።
- ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን በመለየት ማወዳደር።
- በፈርጆች መለየት እና መመደብ።
- ቅጦች እና ግንኙነቶቻቸውን መለየት እና መግለጽ።
- በአንድ ሙሉ ነገር ክፍሎች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን መለየት።

**ትብብር**፦ የቡድኑን ግብ ለመድረስ በውጤታማነት እና በመከባበር መሥራት።

- ከቡድን አባላት ጋር ባለ ግንኙነት ንቁ ሰሚና ተግባቢ መሆንን ማሳየት።
- መግባባትን ለማስፋትና ጥልቀት ለመስጠት በርካታና የተለያዩ አስተያየቶችን ማስተናገድና ማክበር።
- በውጤታማነት ከሌሎች ጋር አብሮ በመስራት የቡድን ሰው የመሆን ዝንባሌ ማሳየት።